Amharic

# ለእንባ ጠባቂ ቅሬታን ማቅረብ

COMMONWEALTH OMBUDSMAN

**የኮመን ዌልዝ እንባ ጠባቂ (Ombudsman) በአውስትራሊያ መንግሥት የአስተዳደር ተቋሞችና በተወሰኑ የግል መስክ በተሰማሩ ድርጅቶች ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ይመረምራል።**

## የእንባ ጠባቂው እንዴት ሊረዳዎ እንደሚችል

ያለአግባብ ተስተናግጄአለሁ ብለው የሚያስቡ ከሆነ፣ ለእናባ ጠባቂ ቢሮ ቅሬታዎን ማቅረብ ይችላሉ።

ምርመራ የሚካሄድባቸው ቅሬታዎች የሚከተሉት ናቸው፡

> **ተቋሞች** — እንደ የድጎማና የልጆች ድጋፍ ክፍያዎች፣ ሃገር አቀፍ ጤናና የመጓጓዣ አገልግሎቶችና ሌሎች ሃላፊነት ያለበቻው አገልግሎቶችን።

> **አገልግሎቶች** — ለአውስትራሊያ መንግሥት በግል ኮንትራት የሚቀርቡ አገልግሎቶችን።

> **የመረጃ ነፃነት (FOI)** — መረጃን በነፃ (FOI) የመስጠት ጥያቄ የአፈጻጸም መጓተትን።

> **የአውስትራሊያ ሃገር አቀፍ ፖሊስ (AFP)** — የአውስራሊያን የሃገር አቀፉን የፖሊስ አባላትን እና ድርጅቱን በተመለከተ ስለፖሊሲዎች፣ ልምዶችና ስርዓቶችን።

> **የፖስታ ኢንዱስትሪ** — በፖስታ ኢንዱስትርሪ በእንባ ጠባቂ ቅንብር (PIO) የተመዘገቡ የአውስትራሊያ ፖስታና የግል ፖስታ አከፋፋዮችን።

> **የግል የጤና መድህን** — የጤና ድጎማ አባላት፣ የጤና ድጎማዎች፣ የግል ሆስፒታሎች ወይም የህክማና ሠራተኞችን። ቅሬታው የጤና መድህን እቅድን የተመለከተ መሆን አለበት።

> **የውጭ ሃገራት ተማሪዎች** — በአውስትራሊያ በመማር ላይ ያሉና የቀድሞ የውጭ ሃገር ተማሪዎች መድህንን በተመለከተ ከግል ትምህርት ቤቶች፣ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች የሚነሱ ችግሮችን።

> **የአውስትራሊያ ካፒታል ግዛቶች (ACT)** — የአውስትራሊያ ካፒታል ግዛቶች የመንግሥት አስተዳደራዊ እርምጃዎችን።

## ቅሬታን እንዴት እንደሚያቀርቡ

በመጀመሪያ፣ ቅሬታዎን ለመፍታት የሚመለከተውን ድርጅት የቅሬታ ተመልካች ክፍልን በመጠየቅ ችግሩን ለመፍታት ይሞክሩ። ድርጅቱ የሰጠዎት መልስ ያላረካዎት ከሆነ እኛን ይገናኙን።

## ቅሬታዎን ወደኛ ሲያቀርቡ ምን ይደረጋል?

ቅሬታዎን በጥንቃቄና በተቻለ ፍጥነት እናየዋለን። ተጨማሪ መረጃ ልንጠይቅዎ እንችላለን፤ እንደ ደብዳቤዎች ወይም ሌሎች ሰነዶች፣ ወይም ቅሬታውን በጽሑፍ እንዲያቀርቡ እንጠይቅዎታለን።

## ይገናኙን

### በስልክ

በ **1300 362 072** ከ 9 am እስከ 5 pm (AEDT) ከሰኞ እስከ አርብ።

### በመስመር ላይ

**www.ombudsman.gov.au**ን ይጎብኙ።

### በጽሑፍ

GPO Box 442, Canberra ACT 2601

## ቅሬታዎን ለማቅረብ በመርዳት ላይ ያሉት አገልግሎቶች።

እንግሊዝኛ መናገር የማይችሉ ግለሰብ ከሆኑ፣ በትርጉምና በአስተርጓሚ አገልግሎት በኩል (TIS)፣ በስልክ ቁጥር፣ **131 450**። የመስማት፣ የማየት ወይም የመነጋገር ችግር ካለብዎ፤ የቲቲዋይ (TTY) አገልግሎት በሃገር አቀፉ የቅብብሎሽ አገልግሎት (National Relay Service) በኩል፣ በስልክ ቁጥር፣ **133 677** አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ።

**የእንባ ጠባቂ አገልግሎቶች በነፃ የሚሰጡ አገልግሎቶች ናቸው።**